# በኢትዮጵያ የንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት
# የኢንፎርሜሽንና ኮርፖሬት ኮሙኒኬሽን ዳይሬክቶሬት
## የሚዘጋጅ ወርሃዊ ዲጂታል መጽሔት

ግንቦት/2017 ዓ.ም

ማውጫ

የምርጫ ቦርድ አመራሮች መልማይ ኮሚቴ ----1
የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክት------------1
የዶክተር ካሳሁን ጎፌ መልዕክት------------2
የምክክር ኮሚሽን ------------3
13ኛው የኦሮሚያ የልምድ ልውውጥ------------3
ከዶክተር አብዱልሐኪም ጋር ውይይት------------4
የዛይድ ዘላቂነት ሽልማት------------4
ከታይላንድ አምባሳደር ጋር ውይይት------------5
ንግድ ምክር ቤቶች ሽልማት------------6
ዶክተር ቀነኒሳ ግንዛቤ ማስጨበጫ------------7
የልምድ ልውውጥ መድረክ ዙሪያ ውይይት ----8
የኢትዮጵያ- ቻይና የቢዝነስ ትብብር ጉባኤ-----9
ከUN WOMEN ተወካዮች ጋር ውይይት-----10
የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን ሴሚናር------------11
ከአዲስ ቻምበር ጋር ውይይት------------12
በሳይበር ደህንነት ዙሪያ ስልጠና ------------12
አትክልትና ፍራፍሬ አምራች ላኪዎች ውይይት-13
የደረጃዎች እንስቲትዩት የቦርድ ስብሰባ------14
የምርጫ ቦርድ እጩ መልማይ ኮምቴ------14
ስልጠና የባለሙያዎችንአቅም------------15
ጥራጥሬና የቅባት እህሎች ላኪዎች ማህበር----16
Breakthrough Trading ማኅበር ------------17

ለመላው የእስልምና እምነት ተከታዮች

እንኳን ለ1446ኛው ዓመተ- ሂጅራ የዒድ አል-አድሃ(አረፋ) በዓል በሰላም አደረሳችሁ!

በዓሉ የሰላም፣ የመተሳሰብና የአንድነት እንዲሆንላችሁ እመኛለሁ።

ሰብስብአባፊራ አባጆቢር
የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት




## የምርጫ ቦርድ አመራሮች መልማይ ኮሚቴ ሪፖርታቸውን ለክቡር ጠቅላይ ሚንስትር ዐቢይ አሕመድ አቅርበዋል።

የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ፕሬዚደንት ሰብስብ አባፊራ አባጆቢር የሚሳተፉበት የምርጫ ቦርድ አመራሮች መልማይ ኮሚቴ ሪፖርታቸውን ለክቡር ጠቅላይ ሚንስትር ዐቢይ አሕመድ አቅርበዋል።







## የንግድና ዘርፍ ማኅበራትና የንግዱ ማኅበረሠብ ያላቸውን ልምድና ተሞክሮ መለዋወጣቸው ያላቸውን ጥንካሬ ለማሥፋትና ለሀገራዊ የኢኮኖሚ ለውጥ ትልቅ ሚና እንዳለው የንግድና ቀጣናዊ ትሥሥር ሚኒስትሩ ዶክተር ካሣሁን ጎፌ ገለጹ።

ሚኒስትሩ ይህን ያሉት በሸገር ከተማ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት አዘጋጅነት በተካሄደው 13ኛው ኦሮሚያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የልምድ ልውውጥ መድረክ በአፍሪካ አመራር ልህቀት አካዳሚ ተገኝተው ባደረጉት ንግግር ነው።





በመድረኩ ከመላው የሀገሪቱ ክፍሎች የተውጣጡ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ተወካዮች እና የንግዱ ማኅበረሠብ የተገኙ ሲሆን ይህም ሊበረታታ የሚገባው መሆኑን ጠቅሠዋል ሚኒሥትሩ።

ንግድ ድንበር ተሻጋሪ ጠንካራ ኢኮኖሚያዊ ግንኙነት እንዲኖር ትልቁ መሣሪያ ነው ያሉት ዶክተር ካሣሁን ጎፌ ለዚህም እንደ አፍሪካ ነጻ የንግድ ቀጣና ሥምምነት ትግበራ ካሉ አሠራሮች ተጠቃሚ ለመሆን የግሉ ዘርፍ ሚና የማይተካ ነው ብለዋል።

የግሉ ዘርፍ ኢኮኖሚው ላይ ሚናውን እንዳይጫዎት የሚይዙ ችግሮችን ለመቅረፍ መንግሥት የፖሊሢ እና የህግ ማሻሻያ ሥራዎችን መሥራቱንም አብራርተዋል።

የጅምላ እና የችርቻሮ እንዲሁም ሌሎች የኢንቨሥትመንት አማራጮች ለውጭ አካላት ክፍት የተደረጉት የውጭ ተሞክሮን ለማላመድና ተጠቃሚነት





መሆኑንም ገልጸዋል።

በሌላ በኩል የልምድ ልውውጥ መድረኩ ከክልል አልፎ በሀገር አቀፍ ደረጃ እውቀት እና ልምድን ለማሥፋት እና ብፐትብብር ለመሥራት እንደ ተሞክሮ የሚወሠድና ትልቅ አሥተዋጽኦ እንዳለው የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕራዚዳንት እና የኦሮሚያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚደንት አቶ ሰብስብ አባፊራ አባጆቢር ገልጸዋል።

13ኛው የኦሮሚያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የልምድ ልውውጥ መድረክም ላለፉት ዓመታት የሚያጋጥሙ ተግዳሮቶችን ለማሥወገድ እና የንግዱ ማኅበረሠብ በኦኮኖሚው ውሥጥ ያለውን አበርክቶ ለማሣደግ ሲካሄድ መቆየቱን ፕሬዚዳንቱ አንሥተዋል።

ለዝግጅቱ መሣካት አሥተዋጽኦ ያደረጉ አካላትን ያመሠገኑት አቶ ሰብስብ አባፊራ  በቀጣይም ማኅበራት ከመቼውም ጊዜ በበለጠ በጋራ መሥራትእንዳለባቸው መልእክታቸውን አሥተላልፈዋል።

የሸገር ከተማ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት እና የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የቦርድ አባል መጋቢ ሥርዓት ቀሲስ ታየ ለታ በበኩላቸው ይህ የልምድ ልውውጥ መድረክ ጠንካራ አሠራሮችና ልምዶች እንዲጠናክር እንዲሁም የሚያጋጥሙ እንቅፋቶችን ለመቅረፍ እና የግሉ ዘርፍ በኢኮኖሚው ውሥጥ የመሪነት ሚናውን እንዲወጣ የሚያሥችል መሆኑን አብራርተዋል።በዚህ የልምድ ልውውጥ መድረክ ከፍተኛ የመንግሥት የሥራ



ኃላፊዎች፣ የሀገራት አምባሣደሮች፣ የክልል የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የቦርድ አባላት እና ተወካዮች እንዲሁም የግሉ ዘርፍ ተወካዮች ታድመዋል።

## ኢትዮጵያ እየመከረች ነው::

**የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን የምክክር መድረክ ፤ የፌዴራል ባለድርሻ አካላት፤ በአዲስ አበባ ሚሊኒየም አዳራሽ የተካሄደ ሲሆን በመድረኩም የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት የቦርድ አባላት ተሳትፎ አድርገዋል ::**









## 13ኛው የኦሮሚያ ክልል የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የልምድ ልውውጥ መድረክ ዙሪያ ውይይት ተካሄደ።

**በሸገር ከተማ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት አዘጋጅነት በሚካሄደው 13ኛው የኦሮሚያ ክልል የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የልምድ ልውውጥ መድረክ ዙሪያ ውይይት ተካሄደ።**

መድረኩ በሸገር ከተማ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት አዘጋጅነት ግንቦት 23/2017 በሱሉልታ የአፍሪካ ልህቀት አመራር አካዳሚ የተካሄድ ሲሆን ውይይቱም የዚሁ አካል ነበር።

በውይይቱም የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት አቶ ሰብስብ አባፊራ፣ የምክር ቤቱ ዋና ጸሐፊ ዶክተር ቀነኒሣ ለሚ፣ የኦሮሚያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ምክትል ፕሬዚደንት አቶ መገርሣ ረጋሣን ጨምሮ የክልሎች የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት አመራሮችና ከኦሮሚያ ክልል የተለያዩ ከተሞች የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የተወጣጡ አመራሮች ተገኝተዋል።

አቶ ሰብስብ አባፊራ አባጀቢር የምክክር መድረኩን አሥመልክተው በዋዜማው በተካሄደ ውይይት ላይ ባሥተላለፉት መልእክት የጠንካራ ምክር ቤቶች ተሞክሮ ወደ ሌሎች ምክር ቤቶች እንዲሥፋፋ እና እንዲጠናከር በሚል የልምድ ልውውጥ መድረኩ መጀመሩን ጠቁመው ላለፉት ዓመታት መቀጠሉንና ዘንድሮም ለ13ኛ ጊዜ እንደሚካሄድ ገልጸዋል።

ምክር ቤቶች ብቁ ሥልጠና መሥጠት እንዲችሉ፣ አድቮኬሲ ላይ እንዲሠሩ፣ የአባላትን አቅም እንዲያሣድጉ፣ ጥንካሬ እንዲስፋፋ ለማድረግ የልምድ ልውውጡ ትልቅ ሚና እንዳለው ገልጸዋል።

መድረኩ ከኦሮሚያ ባለፈ ለሁሉም ክልሎች ልምድ እንዲለዋወጡ እድል የፈጠረ መሆኑን በመጠቆም ንግድ ሀይማኖት፣ ዘርና ድንበር የሌለው በመሆኑ ለሁሉም የንግዱ ማኅበረሰብ ትልቅ ሚና ያለው ነው።

የኦሮሚያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት በአዋጅ የተሠጡትን ተልእኮዎች ግብ ለማድረስ የግሉ ዘርፍ በ2 የስትራቴጂክ ዘመናት ጠንካራ እና ኢኮኖሚውን የሚመራ እንዲሆን እየሠራ ነው ብለዋል።

ምክር ቤቶች የተጣለባቸውን ኃላፊነት በአግባቡ እንዲወጡ እና ውጤታማ ሥራ እንዲሠሩ ለማድረግ በየዓመቱ የልምድ ልውውጥ መድረኩ እየተዘጋጀ መቀጠሉን በዋዜማው በተዘጋጀ ውይይት ላይ የሸገር ከተማ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚደንት መጋቢ ሥርዓት ቀሲስ ታየ ለታ ገልጸዋል።

13ኛው የልምድ ልውውጥ መድረክም ከፍተኛ የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች፣ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤቶች አመራሮችና የግሉ ዘርፍ ተወካዮች በተገኙበት ነው የተካሄደው።



## ከንግድ እና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስትር ደኤታ ክቡር አብዱልሃኪም ሙሉ (ዶ/ር ) ጋር ዉይይት

**ከንግድ እና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስትር ደኤታ ክቡር አብዱልሃኪም ሙሉ (ዶ/ር ) ጋር የክልል እና የከተማ ንግድ እና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤቶች አደረጃጀትን ማጠናከር በሚቻልባቸው ጉዳዮች ዙርያ ዛዉይይት መደረጉን የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚደንት ሰብስብ አባፊራ አባጆቢር ገለጹ ::**





በውይይቱም ክቡር ሚኒስትር ደኤታው መንግስት የግሉን ዘርፍ ለማጠናከር እንዲቻል ብዙ ስራዎችን ከንግድ ምክር ቤቶች ጋር እየሰራ መሆኑን ጠቅሰው፤ በቀጣይም በየደረጃ ያሉት ምክር ቤቶች እንዲጠናከሩና የሚጠበቅባቸውን ሚና እንዲወጡ ሚኒስቴር መ/ቤታቸው የሚጠበቅበትን ሁሉ እንደሚያደርግም አረጋግጠዋል ::

**የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ዋና ጸሐፊ ዶ/ር ቀነኒሳ ለሚ (ተባባሪ ፕሮፌሰር) የዛይድ የዘላቂነት ሽልማት ተወካዮችን በጽህፈት ቤታቸው ተቀብለው አነጋግረዋል።**





ስትራቴጂካዊ አቅጣጫዎች እና የትብብር መስኮች ዋና የውይይት ርዕሰ ጉዳዮች ሲሆኑ ከድርጅቱ ዋና ትኩረት አቅጣጫዎች ጋር በማስተሳሰር ሁለቱም ወገኖች በጋራ የሚችሉባቸውን መንገዶች ዙሪያ ተወያይዋል።

የዛይድ የዘላቂነት ሽልማት ተወካዮች እንዳብራሩትም በሀገር አቀፍ ደረጃ በጤና፣ በምግብ፣ በኢነርጂ፣ በውሃ፣ በአየር ንብረት ለውጥ እርምጃዎች እና ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች እንዲሁም መካከለኛና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች (SMEs) በሽልማቱ ውድድር እንደሚሳተፉ ተጠቁሟል።



የዛይድ ዘላቂነት ሽልማት የግሉ ሴክተሩን ቀጣይነት ያለው እድገት በማስተዋወቅ እና ለሰፊ ማህበረሰባዊ እና አካባቢያዊ ግቦች አስተዋፅኦ ለማድረግ ፍላጎት እንዳለው ተጠቁሟል።

የተባበሩት አረብ ኢሚሬቶች መስራች ሼክ ዛይድ ቢን ሱልጣን አል ናህያንን ለማሰብ የተቋቋመው ሽልማቱ ለአለም አቀፍ ፈተናዎች ችግሮች መፍትሄዎችን የሚያቀርቡ ድርጅቶችን እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን በመደገፍና እውቅና በመስጠት የሚሰራ ተቋም ነው።

**የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ምክትል ፕሬዚዳንት ዶክተር ዓይናለም አባይነህ በኢትዮጵያ ከታይላንድ አምባሳደር ሞራኮት ጃንግማቱኮርን ጋር ተወያዩ።**

የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ምክትል ፕሬዚዳንት ዶክተር ዓይናለም አባይነህ በኢትዮጵያ ከታይላንድ አምባሳደር ሞራኮት ጃንግማቱኮርን ጋር ተወያዩ።

ሁለቱ ወገኖች በሀገራቱ መካከል ስለሚኖረው የኢኮኖሚ እና ኢንቨስትመንት እንዲሁም በቢዝነስ ግንኙነቶች ዙሪያ ነው የተወያዩት።

ዶክተር ዓይናለም አባይነህ ምክር ቤቱ በሚሰራቸው ስራዎች እንዲሁም በኢትዮጵያ ስላሉ መልካም እድችና የሁለቱን ሀገራት የንግድና ኢንቨስትመንት እድሎች ማሳደግ በሚቻልባቸው ጉዳዮች ላይ ለአምባሳደሯ አብራርተውላቸዋል።

አምባሳደር ሞራኮት በበኩላቸው በሁለቱ ሀገራት የግሉ ዘርፍ ተዋናዮች መካከል ያለውን የቢዝነስ የጋራ ተጠቃሚነት ማስፋት እንደሚገባ፤ የሀገራቱ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤቶችም ተቀራርበው መስራት እንደሚገባቸውና ለዚህም በትኩረት እንደሚሰሩ ገልጸዋል።

በውይይቱም የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ምክትል ዋና ጸሐፊ አቶ ጸደቀ ድጋፌ፣ በኬንያ የታይላንድ ኤምባሲ 2ኛ ጸሐፊ ተራዌ ጉራድቶፐን ጨምሮ ሌሎች ተወካዮችም ተገኝተዋል።







**ውጤት ያስመዘገቡ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤቶችና ባለድርሻ አካላት ሽልማት ተበረከተላቸው።**

በ13ኛው የኦሮሚያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የልምድ ልውውጥ ፕሮግራም ላይ ውጤት ላሥመዘገቡ ምክር ቤቶች እንዲሁም ለልምድ ልውውጡ ፕሮግራም የላቀ ተሣትፎ ለነበራቸው ባለድርሻ አካላት ነው ሽልማቱ የተበረከተው።

ሽልማት የተበረከተላቸው ለአባላትና ለንግዱ ማኅበረሠብ በሚሠጧቸው አገልግሎቶች የላቀ አፈጻጸም ላሥመዘገቡ ምክር ቤቶች፣ የክልል የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤቶች፣ የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤቶች፣ ማኅበራት፣ ለ13ኛው የልምድ ልውውጥ ፕሮግራም በአጋርነት ለሠሩ ባለድርሻ አካላት ነው።

ሽልማቱን ያበረከቱ የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት እና የኦሮሚያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት አቶ ሰብስብ አባፊራ አባጆቢር፣ የሸገር ከተማ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚደንት መጋቢ ሥርዓት ቀሲስ ታየ ለታ፣ የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ምክትል ፕሬዚዳንት ዶክተር ዓይናለም አባይነህ ናቸው።

የተበረከተውም የዋንጫ፣ ጋቢን ጨምሮ ባህላዊ መገልገያ እንዲሁም የሠርተፊኬት ሽልማት ሲሆን የኢራን ኤምባሲም ከሸገር ከተማ ጋር በሚያደርጋቸው የትብብር ሥራዎች ተሸላሚ ሆኗል።

የሸገር ከተማ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት፣ የጅማ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት እንዲሁም የነቀምቴ ከተማ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ባስመዘገቡት ውጤት የልዩ ዋንጫ ተሸላሚ ሆነዋል። 14ኛው የኦሮሚያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የልምድ ልውውጥ ፕሮግራም በጅማ ከተማ እንደሚዘጋጅም በዝግጅቱ ላይ ተገልጿል።



















**የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ዋና ፀሐፊ ዶክተር ቀነኒሳ ለሚ (ተባባሪ ፕሮፌሠር) "Leading Chamber to Success: Global Context and Local Practices" በሚል ርዕስ የግንዛቤ ማሥጨበጫ ጽሑፍ አቅርበዋል።**



በአፍሪካ አመራር ልህቀት አካዳሚ በተካሄደው 13ኛው የኦሮሚያ ንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የልምድ ልዉዉጥ ፕሮግራም ላይ ጽሑፋቸውን ያቀረቡት ዶክተር ቀነኒሳ ለሚ በተለይም ከዓለም



ነባራዊ ሁኔታ በመነሳት በተቋም ግንባታ ላይ ትኩረት



በማድረግ የምክር ቤቶችን አቅም ከፍ ማድረግ ጥቅማቸውን ለማሥከበር፣ የአድቮኬሲ እና ምርምር ሥራዎችን ለመሥራትና ለሌሎችም የቢዝነስ ጉዳዮች የላቀ ፋይዳ እንዳለው አንሥተዋል።

ዋና ጸሐፊው የሌሎች ሀገራትን ተሞክሮ በመጥቀስ የምክር ቤቶችን ዓለም አቀፍ አደረጃጀትና አሠራሮችን አብራርተዋል።

ዓለም አንድ በሆነበት በዚህ ወቅት የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤቶች አሠራር ከሌሎች ሀገራት አሠራር ጋር የተቀናጀ እና ለሀገር ኢኮኖሚ የላቀ አበርክቶ እንዲኖረው ለማድረግ መሥራት እንደሚገባ ገልጸዋል።

ለዚህም የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤቱ ሪፎርም በማካሄድ ለውጥ ለማምጣት ከመቼውም ጊዜ በበለጠ እየሠራ ነዉ።



**በሸገር ከተማ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት አዘጋጅነት በሚካሄደው 13ኛው የኦሮሚያ ክልል የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የልምድ ልውውጥ መድረክ ዙሪያ ውይይት ተካሄደ።**



መድረኩ በሸገር ከተማ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት አዘጋጅነት ግንቦት 23/2017 በሱሉልታ የአፍሪካ ልህቀት አመራር አካዳሚ የሚካሄድ ሲሆን ከዚህ ጋር በተያያዘ ነው ውይይቱ የተካሄደው።




በውይይቱም የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት አቶ ሰብስብ አባፊራ፣ የምክር ቤቱ ዋና ጸሐፊ ዶክተር ቀነኒሣ ለሚ፣ የኦሮሚያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ምክትል ፕሬዚደንት አቶ መገርሣ ረጋሣን ጨምሮ የክልሎች የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት አመራሮችና ከኦሮሚያ ክልል የተለያዩ ከተሞች የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የተውጣጡ አመራሮች ተገኝተዋል።



አቶ ሰብስብ አባፊራ አባጀቢር የምክክር መድረኩን አሥመልክተው በዋዜማው በተካሄደ ውይይት ላይ ባሥተላለፉት መልእክት የጠንካራ ምክር ቤቶች ተሞክሮ ወደ ሌሎች ምክር ቤቶች እንዲሥፋፋ እና እንዲጠናከር በሚል የልምድ ልውውጥ መድረኩ መጀመሩን ጠቁመው ላለፉት ዓመታት መቀጠሉንና ዘንድሮም ለ13ኛ ጊዜ እንደሚካሄድ ገልጸዋል።

ምክር ቤቶች ብቁ ሥልጠና መሥጠት እንዲችሉ፣ አድቮኬሲ ላይ እንዲሠሩ፣ የአባላትን አቅም እንዲያሣድጉ፣ ጥንካሬ እንዲስፋፋ ለማድረግ የልምድ ልውውጡ ትልቅ ሚና እንዳለው ገልጸል።

መድረኩ ከኦሮሚያ ባለፈ ለሁሉም ክልሎች ልምድ እንዲለዋወጡ እድል የፈጠረ መሆኑን በመጠቆም ንግድ ሀይማኖት፣ ዘርና ድንበር የሌለው በመሆኑ ለሁሉም የንግዱ ማኅበረዝሰብ ትልቅ ሚና ያለው ነው።

የኦሮሚያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት በአዋጅ የተሠጡትን ተልእኮዎች ግብ ለማድረስ የግሉ ዘርፍ በ2 የሥትራቴጂክ ዘመናት ጠንካራ እና ኢኮኖሚውን የሚመራ እንዲሆን እየሠራ ነው ብለዋል።




ምክር ቤቶች የተጣለባቸውን ኃላፊነት በአግባቡ እንዲወጡ እና ውጤታማ ሥራ እንዲሠሩ ለማድረግ በየዓመቱ የልምድ ልውውጥ መድረኩ እየተዘጋጀ መቀጠሉን በዋዜማው በተዘጋጀ ውይይት ላይ የሸገር ከተማ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚደንት መጋቢ ሥርዓት ቀሲስ ታየ ለታ ገልጸዋል።13ኛው የልምድ ልውውጥ መድረክም ከፍተኛ የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች፣ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤቶች አመራሮችና የግሉ ዘርፍ ተወካዮች በተገኙበት ነው የሚካሄደው።

## የኢትዮጵያ- ቻይና (ሺጂያንግ) የቢዝነስ ትብብር ጉባኤ (Ethio-China Business cooperation and exchange conference ) በአዲስ አበባ ተካሄደ ።

የኢትዮጵያ- ቻይና (ሺጂያንግ) የቢዝነስ ትብብር ጉባኤ (Ethio-China Business cooperation and exchange conference ) በአዲስ አበባ ተካሄደ ።

በዚህ ጉባኤ የውጭ ጉዳይ ሚኒሥትር ደኤታ አምባሣደር ሀደራ አበራ፣ በኢትዮጵያ የቻይና አምባሣደር ቼን ሀይ፣ የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ምክትል ፕሬዚደንት ዶክተር ዓይናለም አባይነህ፣ የኢንዱሥትሪ ሚኒሥትር ደኤታ አቶ ታረቀኝ ቡሉልታን ጨምሮ ከፍተኛ የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች፣ የቻይና (ሺንጂያንግ) እና የኢትዮጵያ ኩባንያዎች ተወካዮች ተገኝተዋል።





የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ከቻይናው ዓለም አቀፍ የንግድ ፕሮሞሽን ምክር ቤት ( CCPIT) - ሺጂያንግ ጋር የመግባቢያ ሥምምነት ተፈራርመዋል።



በአዲስ አበባ ሸራተን አዲስ ሆቴል የተካሄደው ሥምምነቱ የሁለቱን ሀገራት የቢዝነሥ ትብብር ወደ ላቀ ደረጃ ከፍ እንደሚያደርገው ይታመናል።

ከዚሁ ጎን ለጎን የኢትዮጵያ ኩባንያዎችም ከቻይና (ሺጂያንግ) አቻዎቻቸው ጋር በጋራ ለመሥራት የሚያሥችላቸውን ሥምምነት




ተፈራርመዋል።

## የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ዋና ጸሐፊ ዶክተር ቀነኒሳ ለሚ (ተባባሪ ፕሮፌሰር) ከUN WOMEN ተወካዮች ጋር ተወያዩ።





ሁለቱ አካላት በጋራ በሚሰሩባቸው ጉዳዮች ዙሪያ በተለይም በሴቶች አቅም ግንባታና ሌሎች ጉዳዮች ላይ እንደሚሰሩ ተወያይተዋል።

የምክር ቤቱ ዋና ጸሐፊ ዶክተር ቀነኒሳ ለሚ ምክር ቤቱ ለሴቶች፣ ወጣቶች እና አካል ጉዳተኞች ልዩ ትኩረት በመስጠትና የስራ ክፍል በማቋቋም እየሰራ መሆኑን ለተወካዮቹ አብራርተውላቸዋል።

የማኅበረሰቡ ግማሽ አካል የሆኑት ሴቶችን አቅም ከፍ ለማድረግ ምክር ቤቱ ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ትኩረት በመስጠት ከልማት አጋሮች እና ከመንግስት ተቋማት ጋር በትብብር እየተሰራ መሆኑን አንስተዋል ።



የUN WOMEN የኢኮኖሚ አቅም ግምባታ (WEE) ፕሮግራም ኃላፊ ስመኝ ኩማ በበኩላቸው የሴቶችን አቅም ለማጎልበት በአቅም ግንባታ እና ግንዛቤ ማሻሻል፤ የሴቶችን ተሳትፎ በሚሹ የበጀት፣ የግዥ እና የኦዲት በመሳሰሉ ጉዳዮች፣ በአነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ኢኮኖሚ ልማት እንዲሁም በአፍሪካ ነጻ የንግድ ቀጣና ስምምነት ትግበራ ዙሪያ በጋራ መስራት እንደሚቻል አብራርተዋል።



ሁለቱ አካላት ከሌሎች የመንግስት ተቋማት ጋር በመተባበር የሚያዘጋጁት የሴቶች አቅም ግንባታ ላይ ያተኮረ ፎረም እንደሚካሄድም ተጠቁሟል።

## የኢትዮጵያ ንግድና የዘርፍ ማህበራት ም/ቤት ከተባበሩት መንግስታት የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን (UNECA) ጋር በመተባበር የቢዝነስ ሴሚናር አካሄደ።

የኢትዮጵያ ንግድና የዘርፍ ማህበራት ም/ቤት ከተባበሩት መንግስታት የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን (UNECA) ጋር በመተባበር የቢዝነስ ሴሚናር አካሄደ።

ሴሚናሩ ያተኮረዉ የአገር ዉስጥ አቅራቢ ድርጅቶች በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የግዥ ህጎች ላይ ተገቢዉ ግንዛቤ ኖሯቸዉ UNECA በሚያወጣቸዉ የተለያዩ ጨረታዎች ላይ ብቁ ተወዳዳሪዎች እንዲሆኑ ማስቻል ላይ ነዉ።








በሴሚናሩ ላይ የመክፈቻ ንግግር ያደረጉት የኢትዮጵያ ንግድና የዘርፍ ማህበራት ም/ቤት ምክትል ፕሬዚዳንት ዶ/ር ዓይናለም አባይነህ የግሉ ዘርፍ ድምፅ የሆነዉ የኢ/ን/ዘ/ማ/ም/ቤት የግሉ ዘርፍ በአገሪቱ የኢኮኖሚ ዕድገት ዉስጥ የመሪነቱን ሚና እንዲኖረዉ እየሰራ መሆኑን ገልፀዉ በተለይም በአፍሪካ አህጉራዊ ነፃ የንግድ ቀጣና ዉስጥ ተገቢዉን ቦታ እንዲይዝና ተገቢዉን ሚና እንዲጫወት ከሚመለከታቸዉ አካላት ጋር እየሰራን ነዉ ብለዋል።





ይህ የዛሬዉ የቢዝነስ ሴሚናርም የግሉን ዘርፍ የተወዳዳሪነት አቅምን ለማጎልበት ታስቦ የተዘጋጀ ነዉ ብለዋል። የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ም/ቤት ዋና ፀሐፊ ዶ/ር ቀነኒሳ ለሚ(ተባባሪ ፕሮፌሰር) በበኩላቸዋዉ በምክር ቤቱ አጠቃላይ ታሪካዊ ዳራ ራዕይና ተልዕኮ እንዳሁም አጠቃላይ የስራ እንቅስቃሴና እያስመዘገበ ባለዉ አበረታች ዉጤቶች ላይ ሰፋ ያለ ማብራርያ ሰጥ ተዋል።





በቢዝነስ ሴሚናሩ ላይ ከተባበሩት መንግስታት ዋና መ/ቤት በድርጅቱ የግዥ መመርያዎች ላይ ለሴሚናሩ ተሳታፊ የግል ዘርፎች በቪድዮ ኮንፈረንስ ማብራርያ ተሰጥቷል።



**የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ሰብስብ አባፊራ አባጆቢር ከአዲስ አበባ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት በጋራ በሚሰሩባቸው ጉዳዮች ዙሪያ ተወያዩ።**

የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ሰብስብ አባፊራ አባጆቢር ከአዲስ አበባ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት በጋራ በሚሰሩባቸው ጉዳዮች ዙሪያ ተወያዩ።



ፕሬዚዳንቱ ከአዲስ አበባ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ወ/ሮ ዘሐራ መሐመድ ጋር ነው በጽሕፈት ቤታቸው የተወያዩት።



በውይይቱም የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት አቶ ሰብስብ አባፊራ አባል ምክር ቤቶችን ለማጠናከርና በጋራ መሰራት ባለባቸውን ጉዳዮች ዙሪያ አብራርተዋል።

አባል ምክር ቤቶች እንዲጠናከሩ ለማስቻል ተቀራርቦ መሰራት ይገባል ያት አቶ ሰብስብ የአሰራር ሂደቶችን በማስተካከል በንግዱ ማኅበረሰብ ተጠቃሚነት ላይ ትኩረት በማድረግ መስራት አስፈላጊ መሆኑንም ጠቅሰዋል።



የአዲስ አበባ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ወ/ሮ ዘሐራ መሐመድ በበኩላቸው ሁለቱ ምክር ቤቶች በመቀራረብ እና በመደጋገፍ መስራት እንዳለባቸው በማንሳት የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት እያደረገ ያለው ድጋፍም የሚበረታታ መሆኑን ገልጸዋል።

በቀጣይም የምክር ቤቶቹን አቅም በሚያሳድጉ እና በሀገራዊ የቢዝነስ እና ኢኮኖሚ ጉዳዮች ዙሪያ በትብብር እንደሚሰራ በውይይቱ ላይ ተነስቷል። የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤትን ወደ ተሻለ ደረጃ ለማሳደግ ሪፎርም ተግባራዊ በማድረግ የአባል ምክር ቤቶችን አቅም በማሳደግ እና የንግዱን ማኅበረሰብ ተጠቃሚ የሚያደርጉ አሰራሮችን እየተተገበረ መሆኑም የሚታወቅ ነው።

**ለኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የማኔጅመንት አባላትና ሰራተኞ በሳይበር ደህንነት ዙሪያ ስልጠና ተሰጠ።**

ስልጠናው የመረጃ ደህንነትን ለመጠበቅና የሳይበር ጥቃትን ለመከላከል በሚያግዙ ዘዴዎች ዙሪያ ያተኮረ ነው።

በኢሜል አጠቃቀም፣ በማኅበራዊ ሚዲያ እንዲሁም በሌሎች የመገናኛ አውታሮች ስለሚፈጸሙ የሳይበር ጥቃቶች እና እነዚህን በቀላሉ መከላከል እንዲሁም ለሚመለከታቸው አካላት በማመልከት የሳይበር ደህንነትን መጠበቅ እንደሚገባም በስልጠናው ላይ ተነስቷል።



## የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤትና የኢትዮጵያ አበባ፣ አትክልትና ፍራፍሬ አምራች ላኪዎች ማህበር የግሉ ዘርፉ በአገር ኢኮኖሚ ውስጥ ሊጫወት በሚገባው ሚና እና ሊኖረው በሚገባ ድርሻ ዙሪያ ተወያዩ፡፡

በኢትዮጵያ የንግድ እና ዘርፍ ማህበራት ም/ቤት ዋና ፀሐፊ ዶ/ር ቀነኒሳ ለሚ (ተባባሪ ፕሮፌሰር) የተመራ የም/ቤቱ የማኔጅመንት አባላት ቡድን አባላቱ ከሆኑት የዘርፍ ማህበራት አንዱ ከሆነው የኢትዮጵያ አበባ አትክልት ፍራፍሬ አምራች ላኪዎች ማበር ማኔጅመንት አባላት ጋር የግሉን ዘርፍ ሚና ከፍ ለማድረግ በቅንጅት መስራት በሚገባቸው ጉዳዮች ላይ ሰፊ ውይይት አድርገዋል፡፡





የኢ/ን/ዘ/መ/ም/ቤት ዋና ፀሐፊ ዶ/ር ቀነኒሳ ለሚ በአሁኑ ወቀት የግሉ ዘርፍ ለአገር አጠቃላይ ኢኮኖሚ ዕድገት እያበረከተ ያለው አስተዋፅኦ ከሚጠበቅበት አኳያ በጣም ዝቅተኛ መሆኑን በማንሳት ይህንን ወደ ተሻለ ደረጃ ለማሳደግ እና ተገቢውን ቦታና ድርሻ እንዲኖረው ለማድረግ የግሉ ዘርፍ ከመንግስት ጋር ተቀራርቦ የሚሰራ የግሉ ዘርፍ ድምፅ በሚገባ እንዲሰማና ምቹ የስራ ከባቢ አግኝቶ ሚናውን እንዲጫወት በአግባቡ የሚወክለው ጠንካራ ተቋም እንደሚያስፈልገው በማንሳት፤ ለዚህ ዓላማ ከተቋቋመ ረጅም ዕድሜ ያስቆጠረው የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ም/ቤት ከወትሮው በተሻለ ሁኔታ ለመስራት እራሱን በአዲስ መልክ አደራጅቶና መዋቅራዊ ለውጥ አድርጎ ወደ ስራ መግባቱን አንስተዋል፡፡

ያደጉ አገራት አሁን ላሉበት ደረጃ የደረሱት የግሉ ዘርፍ ተገቢውን ሚና እንዲጫወት ምቹ ሁኔታ በመፍጠራቸውና የግሉ ዘርፍም ድምፁ በተገቢ ሁኔታ እንዲሰማ በአንድነት በመቆማቸው ነው ያሉት ዶ/ር ቀነኒሳ፣ የአገራችን የግል ዘርፍም በተናጠል ከመንቀሳቀስ በየደረጃው ባሉት ምክር





ቤቶችና ማህበራት በመታቀፍ ሊንቀሳቀሱ ይገባል ብለዋል፡፡

የኢትዮጵያ አበባ ፣ አትክልትና ፍራፍሬ አምራች ላኪዎች ማህበር ዋና ዳይሬክተር አቶ ቴዎድሮስ ዘውዴ በበኩላቸው አሁን ላይ የግሉ ዘርፍ ትክክለኛ ድምፅ ሊሆን የሚችለውና የግሉን ዘርፍ ከመንግስት ጋር ሊያገናኝ የሚችለው አገር አቀፍ ተቋም የኢትዮጵያ ንግድና የዘርፍ ማህበራት ም/ቤ መሆኑን በማንሳት፣ በተለይም ለግሉ ዘርፍ ምቹ የስራ ካባቢን ለመፍጠርና በግሉ ዘርፍ ላይ ቀጥተኛ ተፅዕኖ ሊያሳድሩ በሚችሉ ፖሊስዎች ላይ ከሚመለከታቸው የመንግስት አካላት ጋር የምክክር መድረኮችን በማመቻቸት የግሉ ዘርፍ ድምፅ በአግባቡ እንዲሰማ ከማድረግ አንፃር አሁን ላይ አበረታች ለውጥ መታየቱንና በመንግስት ዘንድ ያለው የም/ቤቱ ተደማጭነትም እየጨመረ መምጣቱን አስረድተዋል፡፡

ማህበራቸውም እንደ አንድ የም/ቤቱ አባል የአባላቱን መብትና ጥቅም ለማስጠበቅ ከም/ቤቱ ጋር ተቀናጅቶ ለመስራት ከወትሮው በተሸለ ሁኔታ ዝግጁ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

ሁለቱ ተቋማት በጋራ የሚሰሯቸውን ተግባራት ለይቶ በማውጣት የትግበራ መርሐ ግብር የሚያዘጋጅ የጋራ ታስክ ፎርስም አቋቁመዋል፡፡

## የኢትዮጵያ ደረጃዎች እንስቲትዩት 2ተኛ ዙር መደበኛ የቦርድ ስብሰባ

የኢትዮጵያ ደረጃዎች እንስቲትዩት 2ተኛ ዙር መደበኛ የቦርድ ስብሰባዉን በቦርድ ሰብሳቢው በክቡር የንግድና ቀጣናዊ ሚ/ር በዶ/ር ካሣዉን ጎፌ ሰብሳብነት በንግድና ቀጠናዊ ሚንስቴር አደራሽ ተካሂዷል ፡፡








## የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ፕሬዚደንት ሰብስብ አባፊራ አባጆቢር የብሔራዊ የምርጫ ቦርድ እጩ መልማይ ኮምቴ ውስጥ ተሳትፎ እያደረጉ ነው።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ አባላት ዕጩ መልማይ ኮሚቴን ቀደም ሲል መሰየማቸው የሚታወቅ ነው ፡፡



በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግሥት አንቀጽ 102 እና በኢትዮጵያ ምርጫ ቦርድ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 133/2011 አንቀጽ 5(1) መሠረት ከመጋቢት 17 2017 ጀምሮ የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ፕሬዚደንት ሰብስብ አባፊራ አባጆቢር የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ አባላት ዕጩ መልማይ ኮሚቴ አባል ሆነው መሰየማቸው ይታወሳል።





## ስልጠና የባለሙያዎችን አቅም በመገንባት የተቋማትን አፈጻጸም ከፍ እንደሚያደርግ የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ዋና ጸሐፊ ዶክተር ቀነኒሳ ለሚ (ተባባሪ ፕሮፌሰር) ተናገሩ።

ስልጠና የባለሙያዎችን አቅም በመገንባት የተቋማትን አፈጻጸም ከፍ እንደሚያደርግ የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ዋና ጸሐፊ ዶክተር ቀነኒሳ ለሚ (ተባባሪ ፕሮፌሰር) ተናገሩ።







ለምክር ቤቱ የማኔጅመንት አባላትና ሰራተኞች በሳይበር ደህንነት እና በስትራቴጂክ እቅድ ዙሪያ ሲሰጥ የነበረው ስልጠና ተጠናቋል።

በስልጠናው ማጠናቀቂያ ላይም መሰል ስልጠናዎች እና የአቅም ግንባታ ስራዎች የምክር ቤቱን የሪፎርም ተግባራት ለማሳካት የላቀ አስተዋጽ እንዳላቸው ገልጸዋል።

ስልጠናውም በዘርፉ ላይ ያላቸውን እውቀት እና ክህሎት ከፍ እንደሚያደርገውም በስልጠናው የተሳተፉ ሰራተኞች ጠቁመዋል። መሰል የአቅም ግንባታ ስልጠናዎች በሌሎችም መስኮች እንደሚሰጡ ሲገለጽ ስልጠናውን ለሰጡት ባለሙያዎች እና ሰልጣኞችም የምስክር ወረቀት ተሰጥቷቸዋል።



## የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ከኢትዮጵያ ጥራጥሬና የቅባት እህሎች ላኪዎች ማህበር ጋር በአባላት የአቅም ግንባታ ዙሪያ አብሮ መስራት በሚያስችሉ ጉዳዮች ላይ ተወያየ።

**የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ከኢትዮጵያ ጥራጥሬና የቅባት እህሎች ላኪዎች ማህበር ጋር በአባላት የአቅም ግንባታ ዙሪያ አብሮ መስራት በሚያስችሉ ጉዳዮች ላይ ተወያየ።**

በኢትዮጵያ ንግድ እና የዘርፍ ማህበራት ም/ቤት ዋና ፀሐፊ ዶ/ር ቀነኒሳ ለሚ (ተባባሪ ፕሮፌሰር) የተመራ የም/ቤቱ





ማኔጅመንት፤ አባል ከሆኑት የዘርፍ ማህበራት አንዱ ከሆነው የጥራጥሬና የቅባት እህሎች ላኪዎች ማህበር የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትና ዋና ስራ አስኪያጅ ጋር በነበረው ውይይት በማህበሩ አባላት የአቅም ግንባታ ዙርያ አብሮ ለመስራት ከስምምነት ደርሰዋል።

የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ዋና ፀሐፊ ዶ/ር ቀነኒሳ ለሚ በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ



ማህበራት ም/ቤት ከወትሮው በተሻለ ሁኔታ ለመስራት እራሱን በአዲስ መልክ አደራጅቶና መዋቅራዊ ለውጥ አድርጎ ወደ ስራ መግባቱን አንስተዋል።

የኢትዮጵያ ጥራጥሬና የቅባት እህሎች ላኪዎች ማህበር ምክትል ፕሬዚዳንት አቶ አሉላ ገ/ሚካኤል በበኩላቸው አሁን ላይ የኢትዮጵያ ንግድና የዘርፍ ማህበራት ም/ቤት የግሉ ዘርፍ ትክክለኛ ድምፅ ሊሆን ወደ ሚያስችለው ቁመና እየመጣ መሆኑን ጠቅሰው ም/ቤቱ የጀመረውን የሪፎርም ስራ አጠናክሮ ከቀጠለ ማህበራቸው የሚጠበቅበትን የአባልነት ግዴታውን እየተወጣ የም/ቤቱን አቅም በአግባቡ ለመጠቀም ዝግጁ መሆኑን





አስረድተዋል።

## **Breakthrough Trading አክሲዮን ማኅበር ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ጋር በመሆን በቀጥታ ሽያጭ ( Direct Selling) ላይ ባካሄደው ጥናት ዙሪያ ከኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ጋር ተወያዩ።**

Breakthrough Trading አክሲዮን ማኅበር ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ጋር በመሆን በቀጥታ ሽያጭ ( Direct Selling) ላይ ባካሄደው ጥናት ዙሪያ ከኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ጋር ተወያዩ።





በቀጥታ ሽያጭ (Direct Selling) ዙሪያ ከሌሎች ተመሣሣይ ሀገራት ጋር ያለውን ተሞክሮ እንዲሁም በኢትዮጵያ ያለውን ነባራዊ ሁኔታ በመቃኘት በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ላይ ሊያመጣ የሚችለው ኢኮኖሚያዊ እና ማሕበራዊ ተጽእኖ በተመለከተ "The Social and Economic Impact of Direct Selling in Ethiopia and its Legal Grounds" በሚለው ጥናት በስፋት ተዳሷል።

የቀጥታ ሽያጭ በኢትዮጵያ ጠንካራ የህግ ማዕቀፍ እንደሚያሥፈልገው የገለጹት ጥናቱ አቅራቢዎቹ ይህም ለተጠቃሚውም፣





ለአምራቹም ሆነ ሻጩ ትክክለኛ ግብይት እንዲኖር ያሥችላል ብለዋል።

በዚህ ሂደት በቀጥታ ሽያጭ የሚያደርጉ ተቋማት ሥትራቴጂ እና ራእይ እንዲሁም ግልጽ እሴት ሊኖራቸው እንደሚገባ፣ የአቅም ግንባታ ፕሮግራም ማውጣት እንዳለባቸው፣ የኮሚሽን ሠራተኞችን የሚቀጥሩ ተቋማት የኮሚሽን እቅድ ማዘጋጀት እንደሚያስፈልጋቸው እንዲሁም የሽያጭ ሥነ ምግባርን በአግባቡ መከታተል እንደሚገባ ተጠቅሷል።

የምርትና አገልግሎትን በጥራትና በመጠን በትክክል ለማቅረብ፣ የተጠቃሚዎችን ደህንነት ለመጠበቅ እንዲሁም ያለ ሶስተኛ ወገን ጣልቃ ገብነት ከገኘው ወደ ተጠቃሚው በተመጣጣኝ ዋጋ ለማድረስ የቀጥታ ሽያጭ ሊበረታታ የሚገባው አካሄድ መሆኑም ተጠቁሟል።

ለዚህ ደግሞ የፖሊሲ ምእቀፍ ሊኖር እንደሚገባ እና ትኩረት የሚሻ ሥለመሆኑም ነው የተጠቆመው።



Breakthrough Trading በጉዳዩ ዙሪያ የግንዛቤ ማሥጨበጫ ሥራዎችን በስፋት ለመሥራት እንዲሁም የፖሊሲ ብሪፊንግ ሥራዎችም በመሥራት፤ ይህም በምክር ቤቱ በኩል ለሚመለከተው የመንግሥት መሥሪያ ቤት እንዲቀርብ ፍላጎት መኖሩ ተጠቅሷል።

በሌሎች ሀገራት ከተለመደው የግብይት ሥርዓት በተሻለ መልኩ የቀጥታ ሽያጭ የቁጥጥር ማእቀፍ (Direct Selling Regulatory Framework) መኖሩን በማንሣት በኢትዮጵያም በተመሣሣይ አሠራሩም ሆነ ህጉ መኖር እንዳለበት ነው የተብራራው።

# የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት










# የግሉ ዘርፍ ድምጽ!



**ዋና አዘጋጅ:-**

**ተሾመ ዋቅጂራ**

**ም/ዋና አዘጋጅ:-**

**ደበበ አበበ**

**አዘጋጅ**

**ስማቸው ተበጀ**

**ፎቶግራፍ**

**ያለምፍሬ በቀለ**

**የንግድ ምክርቤቱ ራዕይ ፣ተልዕኮ ፣ እሴቶች እና ቀዳሚ ስትራቴጂካዊ አምዶች**

## ራዕይ

“በግሉ ዘርፍ የሚመራ ኢኮኖሚና አካታች ዕድገት በሁለት የስትራቴጂክ ዘመናት ውስጥ እውን ሆኖ ማየት”

## ተልዕኮ

“የኢትዮጵያን የግል ዘርፍ በመወከል፣ በመደገፍና ለመብትና ጥቅሙ አድቮኬት በማድረግ፤ ንግድን፣ ኢንቨስትመንትንና ፈጠራን በማስተዋወቅና በማበረታታት አካታች ኢኮኖሚያዊ ዕድገትና ብልፅግናን ማምጣት”

## ዕሴቶች

- ታማኝነት
- ሙያዊ ብቃት
- አባላት ተኮር ምላሽ ሰጪነት
- ትብብራዊ ጥምረት
- ግልፅነት
- ተጠያቂነት
- ማህበራዊ ሃላፊነት

**ቀዳሚ ስትራቴጂካዊ ጉዳዮች (ስትራቴጂካዊ አምዶች)**

1. አድቮኬሲና የፖሊሲ ተፅዕኖ
2. ጠንካራ የአባላት ተሳትፎና ድጋፍ
3. የሀብት ማሰባሰብና በአግባቡ መጠቀም
4. የአቅም ግንባታና ሥርዓት ማሻሻያ
5. ቴክኖሎጂን ማካትት እና ዲጂታል ሽግግር
6. ዘላቂነት ያለው ማኅበራዊ ኃላፊነት
7. ንግድና ኢንቨስትመንት ማስፋፋት
8. ሁሉን-አቀፍ ጉዳዮች (Cross-cutting issues)

**Mexico Square, ECCSA Building**


**The Ethiopian Chamber of Commerce and Secoral Associations (ECCSA)**

ስልክ: +251115514005

ፋክስ: + 251115517699

P. O. Box 517,

ኢ-ሜይል: info@ethiopianchamber.com

ድረ ገጽ: www.ethiopianchamber.com

ቴሌግራም t.me/ethiopiachamber

ትዊተር https://twitter.com/EthiopiaChamber

ፌስ ቡክ: https://www.facebook.com/EthiopianChamber

Youtube: https://www.youtube.com/channel/UCMEZ4TO8dQiIJvk2IQkTxhA

Linkedin(ሊንክዲን):https://www.linkedin.com/company/ethiopianchamber/in